# የሥነ - ጥበባት ትምህርት
# የመምህሩ መምሪያ
# ስድስተኛ ክፍል


**አፋን ኦሮሞ አዘጋጆች** **አፋን ኦሮሞ ኤዲተሮች**

ከበቡሽ ላሜሳ ዳሜ ቶሊና

ላሚ ቤኛ ሊባባ ጃማል

ዳንዳአ ቦጋለ ታደሰ ድንቁ

**በአፋን ኦሮሞ ገምጋሚዎች**

ድርባ ማሞ

ደቀቦ ጉዬ

እስማኤል ሐሳን

**ተርጓሚዎች** **ኤዲተሮች**

እስማኤል ሐሳን ደቀቦ ጉዬ

ሳላማዊት ጣፋ ሙሉቀን አብራሐም

**ግራፊክስ**

ታደሰ ድንቁ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2022

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2022 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# መዉጫ

ይዝት ገጽ


አጠቃላይ መግቢያ ........ iv
ምዕራፍ 1፡ የስነ-ጥበባት ሥራ በህሪያት ........ 1
1.1.መሰረታዊ የስነጥበባት ንድፍ ........ 2
1.2 የሜጀር እና የማይነር ቁልፍ ........ 7
1.3 ስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልም ........ 21
ምዕራፍ 2: የፈጠራ ስራ ችሎታ ........ 26
2.1 ቀለል ያሉ ዜማዎችን በክሌፎች ላይ መፃፍ ........ 27
2.2 የቀለም ቅብ እና የህትመት ንድፍ ........ 35
2.3 የትያትር፣ የፎቶ እና የምስል-ድምፅ (የቪድዮ) የሃሳብ ገለጻ ........ 42
ምዕራፍ 3 የስነጥበባት ታሪካዊና ባህላዊ ተጨባጭ ሁኔታ ........ 45
3.1 ተረት ተረት ስነ-ትያትርን በመተቀም ማሳየት ........ 46
3.2 የባህል ሙዚቃ መሳሪያ እና የባህል ውዝዋዜ ........ 49
3.3 ስነ-ስዕል በመጠቀም ተረትን አስመስሎ ማሳየት ........ 56
ምዕራፍ አራት የስነ-ጥበባት መስብነት ........ 60
4.1. የማህበረሰቡን ሀገር በቀል እስቀት በቲያትር ማድነቅ ........ 60
4.2. የማህበረሰቡን ሀገር በቀል እውቀት በስነ-ጥበብ ማድነቅ ........ 63
4.3. ሀገር በቀል የማህበረሰብን እውቀት በሙዚቃ ማድነቅ ........ 70
ምዕራፍ አምስት የስነ-ጥበባት ግንኙነት ........ 72
5.1. ስነ-ጥበባትን ከሌላው የትምህርት አይነት ጋር ማያያዝ ........ 73
5.2. የስነ-ጥበባት የተፈጥሮ ሀብትን መጠበቅ እና መንከባከብ ጋር ያለው ትስስር ........ 76
5.3. ስነ-ጥበብ ከሌሎች ነገሮች ጋር ያለው ትስስር ........ 81
የሥነጥበባት ትምህርት ሲለበስ ........ 84

# አጠቃላይ መግቢያ

በመማር ማስተማር ሒደት ዉስጥ የእያንዳንዱ ተማሪ የግል ተሳትፎ እንዳይገደብ መምህሩ/ሯ የአባላቱን ተሳትፎ መከታተል፣መርዳት፣መምራት እና ማበረታታት አስፈላጊ ነዉ፡፡ ስለዚህ መምህሩ/ሯ በትምህርቱ ዉስጥ ሁሉም ተማሪዎች ሀሳብ መስጠት፣መወያየት እና በሀሳብ በመከራከር እዉቀት፣ግንዛቤ እና ያላቸዉን ልምድ በመለማመድ የሚፈለገዉ የትምህርት ዉጤት ላይ እንዲደርስ ማድረግ ነዉ፡፡

መምህሩ/ሯ የሥነ-ጥበብን ትምህርት ሲያስተምሩ ፡-መግቢያ፣ገለፃ፣መጨረሻዉን ከማቀዳቸዉ በፊት ሊያደርጉ የሚገባቸዉ ነገሮች በሚገባ ማዘጋጀት እና መተግበር አለባቸዉ፡፡

## I. ትምህርቱን ከማቀድ በፊት፡-

በመማር ማስተማር ሒደት ዉስጥ የሥነ-ጥበባት እዉቀት፣የትምህርቱን ይዘት ግንዛቤ ለማጠንከር እንዲሁም ሞያቸዉን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሻሻሉ መሄድ አለባቸዉ፡፡የተማረ ሰዉ ሁሉ ማንበብ ካቆመ የሚያስተምረዉንም የትምህርት ዓይነት መርሳቱ የማይቀር ነዉ፡፡ስለዚህ የዚህ ክፍል የሥነ-ጥበብ መምህሩን ከዚህ በታች ያሉትን የስራ ድርሻ እና ተጠያቂነት ለመዉሰድ ዝግጁ መሆን አለባቸዉ፡፡

- ለቀኑ የታቀደዉ የትምህርት እቅድ ወይም ለመስተማር የታሰበዉን ርዕስ ማንበብ እና መረዳት፡፡
- ከተማሪዉ መፅሐፍ ዉስጥ ለማስተማር ከታቀደዉ ትምህርት ዉስጥ አጭር ማስታወሻ መያዝ፡፡
- በተማሪዉ መጽሐፍ ዉስጥ የተፃፉት ማስታወሻ ለእለቱ ትምህርት በቂ ካልሆኑ፣ለሥነ-ጥበብ መምህራን የተዘጋጀዉን ከአምስተኛ--ስምንተኛ (5–8) ክፍል ያለዉን ማኑዋል ወይም ከዌብ ሳይት መጽሐፍ ማዘጋጀት አለበት፡፡
- በተማሪዉ መጽሐፍ ምዕራፍ ዉስጥ ያሉትን ሙከራዎች፣ተግባሮች፣መልመጃዎች እና ጥያቄዎችን ሁሉ ቀድሞ መስራት መሞከር እና መለማመድ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## II. በመግቢያ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራት፡-

- ✓ ተማሪዎች የለፈዉን ትምህርታቸዉን በደንብ መማራቸዉን ለማረጋገጥ መምህራኖች ከትምህርቱ ይዘት ጋር የሚገናኙ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ከቀኑ ትምህርት ጋር ማያያዝ አለባቸዉ፡፡በተለያም የተማሪዎችን ጥይቄ የመጠየቅ እና የመመለስ እድል ለተማሪዎች የተለያየ ደረጃ በመስጠት ላልመለሱት ጥያቄ ደግሞ ጎበዝ ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ ለማድረግ ሁሉም ተማሪዎች ስለ ትምህርቱ በሀሳብ እንዲዘጋጁ እና ክፍል ውስጥ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ እና ተሳትፎ ዉድድር ዉስጥ ለመግባት በትምህርታቸዉ ጎበዝ እንዲሆኑ ማበረታታት፡፡

ከዕለቱ ትምህርት ጋር በማያያዝ በቅድሚያ ተማሪዎች ስለትምህርቱ ያላቸዉን ግንዛቤ ለማወቅ አስፈላጊ የሆኑ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ተማሪዎች ሀሳብ እንዲሰጡበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት፡፡በተለይም ጥቅም፣አስፈላጊነት እና አላማ ለተማሪዎቹ ማስተዋወቅ እና ለእለቱ ትምህርት እንዲዘጋጁ ማድረግ አስፈላጊ ነዉ፡፡

## III. በገለፃ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራት፡-

በመማር ማስተማር ሒደት ዉስጥ በትምህርት ገለፃ ጊዜ፡-

- ✓ በትምህርቱ ይዘት እና አላማ ላይ በመመስረት ተማሪዎች በትናንሽ ቡድን በማደራጀት በመወያያ ርዕስ ላይ እንዲወያዩ ማድረግ፡፡
- ✓ ከትምህርቱ ንኡስ አላማ ጋር የሚገናኝ (የሚያያዝ)ዋና የመወያያ ርዕስ ለቡድኑ የተዘጋጀዉን በቡድን እንዲወያዩበት በጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፍ፡፡
- ✓ መምህሩ/ሯ ተማሪዎች በቡድን መካከል ያለዉን እያንዳንዱን የመማር ሒደት መከታተል፣መምራት፣ መርዳት እና በአይኑ መቆጣጠር አለበት/ባት፡፡
- ✓ የእያንዳንዱን ተማሪ እና በክፍል ዉስጥ ያላቸዉን ተሳትፎ መከታተል እና ማበረታታት፡፡
- ✓ በሁለት ወይም በትናንሽ ቡድን የተወያያችሁበትን ወይም የሰራችሁትን ሁሉም የቡድኑ አባላት ተራ በተራ በተለያዩ ትምህርት ዉስጥ እንዲገልፁ እና ተሳትፎአቸዉ እንዲጠናከር ማድረግ ነዉ፡፡

- ✓ ከዉይይት ወይም ከስራ በኋላ ተማሪዎች ያቀረቡትን ዋና ነጥብ በጥቁር ሰሌዳ ላይ መፃፍ፡፡
- ✓ የትምህርቱን ይዘት ከአካባቢያቸዉ ጋር ማያያዝ እና የመርጃ መሳሪያ በመጠቀም የእለቱን ትምህርት መቋጨት፡፡

**IV. በመጨረሻ ላይ የሚከናወኑ ተግባራት፡-**

- ➢ የዕለቱን ትምህርት አላማ ከግብ መድረሱን ለማረጋገጥ የክፍል ሥራ፣የቤት ሥራ፣የፕሮጀክት ሥራ እና የመሳሰሉትን በጥንድ፣በቡድን ወይም በግል እንዲሰሩ ማድረግ፡፡
- ➢ ተማሪዎች ለሰሩት የቤት ስራ እና የክፍል ስራ የሚያስፈልገዉን ግብረ መልስ በጊዜዉ መስጠት፡፡
- ➢ የቤት ስራ፣የክፍል ስራ፣የፕሮጀክት ስራ እና የመሳሰሉትን ተሰጠቷቸዉ መመለስ ላቃታቸዉ ተማሪዎች ልዩ እገዛ ስጣቸዉ፡፡
- ➢ በሚቀጥለዉን ትምህርት ክፍለ ጊዜ ትምህርቱን አንብበዉ እንዲመጡ ምራቸዉ፡፡

# ምዕራፍ 1፡ የስነ-ጥበባት ሥራ በህሪያት

**ለዚህ ምዕራፍ የተሰጠ ክፍለ ጊዜ…………24**

**ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ የትምህርት ውጤቶች፡**

**ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች፡**

የንድፍ ምንነት ይረዳሉ፡፡

- በንድፍና በሌሎች የስነ-ጥበባት አይነቶች መካከል ያለውን ትስስር ያደንቃሉ፡፡
- የንድፍ ስራ በሌሎች የስነ-ጥበባት ስራዎች ውስጥ ያለውን ጠቃሚታ ይረዳሉ፡፡
- የማይነርና የሜጀር ቁልፎችን ለይተው ያውቃሉ፡፡
- ፒችና የቁልፍ ምልክቶችን ይረዳሉ፡፡
- የስነ-ትያትርና ስለ-ፊልም ምንነት ይረዳሉ፡፡
- የትያትር ዝግጅትን ይረዳሉ፡፡
- የትያትር እስክሪፕት መፃፍ ይማራሉ፡፡

**መግቢያ**

ንድፍ የሁሉም ሥራዎች መሠረት ሆኖ አንድ ሰው በስነ-ጥበብ ሥራ ውስጥ በመጀመሪያ ሃሳቡን ንድፍ በመሥራት ያዳብራል፡፡ ንድፍ በአካባቢያችን የሚገኙ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የሆኑ ነገሮችን ትርጉም ባላው መልክ በስዕል ወረቀት ወይም በሌላ ነገር ላይ የምናስቀምጥበት መንገድ ነው፡፡ በአእምሮ የታሰበውን ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ ወረቀት ላይ በስዕል ማስቀመጥ ነው፡፡ ንድፍ ጠጣር በሆኑ መሳሪያዎች ለምሳሌ እርሳስ፣ ከሰል፣ ቾክ፣ ብዕርና የመሳሳሉትን በመጠቀም ይሠራል፡፡

ከዚህ በፊት ስለ ሙዚቃና ውዝዋዜ አለባውያን አይነቶች፣ ክሌፎች ላይ የኖታ ስሞችን መሰየም እና ሙዚቃ በመማር ውስጥ ያለቸውን ጠቃሚታ ተምረቸዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ስለ ሜጀርና ማይነር ቁልፍ፣ ፒች፣ የቁልፍ ምልክቶች ምንነትና ጥቅም ትማራላችሁ፡፡

በተጨማሪም ለትያትር አስፈላጊ የሆኑ የትያትር እስክርፕት አለባውያንን ተምራቸዋል፡፡ እነዚህም ለዚህ ክፍል ደረጃ ትምህርት መሠረት ይሆኑላቸዋል በዚህ ርዕስ ትምህርት ስር

ስለ ስነ-ትያትር ምንነት፣ እስክርፕት፣ ዝግጅት እና የትያትር እስክርፐት እንዴት እንደሚፃፍ የምትማሩ ይሆናል፡፡

**የምእራፉ ዋና ዋና ነጥቦች**

1.1.መሠረታዊ የስነ-ጥበብ ስራዎች ንድፍ (ክፍለ ግዜ 6)

1.2.የሜጀርና ማይነር ቁልፍ (ፒችና የቁልፍ ምልክት እና የሙዚቃ እስታፍ ንድፍ) (ክፍለ ግዜ 5)

1.3. የስነ-ትያትርና የፊልም ጥበባት (ክፍለ ግዜ 6)

1.4. የውዝዋዜ ንድፍ (ክፍለ ግዜ 7)

## 1.1.መሰረታዊ የስነጥበባት ንድፍ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ............6

ተማሪዎች ቢያነስ መጎናፀፍ የሚገባቸው የመማር ብቃት

ከዚህ ርዕስ ትምህርት በኋላ ተማሪዎች

- የንድፍ ምንነት ይናገራሉ፡፡
- የንድፍ ሃሳብ አይነቶችን ይዘረዝራሉ፡፡
- ንድፍ በመጠቀም ቀለል ያሉ ስራዎችን ይሠራሉ፡፡
- ንድፍ ከሌሎች ስነ-ጥበብ አይነቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ያብራራሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

ማዳመጥ

መመልከት

ማሳየት

ልምምድ

የግል፣ የጥንድና የቡድን ውይይት

ገለፃ

ጥያቄና መልስ

የፕሮጀክት ዘዴ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

የልምምድ ቦታ/እስቱድዮ

ቻርቶች

ፖስተር

**የመምህሩ ድርሻ**

ተማሪዎች በእርሳስ ወይም በብዕር ከዚህ በፊት ስዕል አንስተው እንደሆነ ያለቸውን ግንዛቤ በመጠየቅ የምእራፉን ትምህርት መጀመር ይቻላል፡፡ ተማሪዎች ካዚህ በፊት በእርሳስ ያነሱት ስዕል ምን እንደሆነ በቡድን እንድወያዩ ያድርጉ፡፡

በየንዑሳን ርዕሶች ስር ያሉ ተግባራት የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ለመገንዘብ ስለሚረዱ ወደ ገለፃ ከመግባት በፊት ተማሪዎቹ ተወያይተው ሃሰባቸውን እንድገልፁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

ከተሰጡት ተግበራትና ጥያቄዎች የተወሰኑትን እንደ ክፍል ስራና የቤት ስራ እንድሠሩ ማድረግ ይቻላል፡፡

ተማሪዎቹ ለሠሩት ስራ አስፈለጊውን ግብረ-መልስ በጊዜ ይስጡ፡፡

ቢያነስ መነናፀፍ ከሚገባቸው የመማር ብቃት ላይ የደረሱ ተማሪዎችን መበረታታትና የበለጠ ጠንክረው እንድሠሩ መንገር ያስፈልጋል፡፡

ከሚገባቸው የመማር ብቃት ላይ ላልደረሱ ተማሪዎች ደግሞ ተጨማሪ እገዛ ይደረግላቸው፡፡

ተማሪዎች ለሚሠሩት ነገር ሁሉ ግንዛቤና መነሳሳት እንዲኖራቸው ለሠሩት ነገር ሁሉ ውጤታቸው ይመዝገብላቸው፡፡

**ተከታታይ ምዘና**

የግልና የቡድን ፅብረቃ

ፖርትፎሊዮ

የቃል ጥያቄ

የሙከራ ፈተና

ፈተና

የግልና የቡድን ፕሮጀክት

**የተግባር 1 መልስ**

### 1.1.1. ንድፍ

መምህር/ርት ተማሪዎች ሌላ ሰው ስዕልን በእርሳስ (እስክሪብቶ) ሲሰራ አይተው እንደሚያውቁ ወይም እራሳቸው ሰርተው እንደሚያውቁ ጠይቋቸው እና በእርሳስ የሚሳለው ስዕል ምን እንደሆነ በግላቸው ከአሰቡበት በኋላ ለክፍል እንዲያቀርቡ ያድረጉ፡፡ ከተማሪዎች ሀሳብ ከወሰድክ በኋላ ተማሪዎችን አበረታተህ/ሽ ስነ-ንድፍ ትርጉም እና ምንነት ለተማሪዎች አቅርቡ፡፡

ንድፍ ማለት በአካባቢያችን በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ የሚገኝ ነገር ትርጉም ባለው ሁኔታ በወረቀት እና በሌሎች ነገር ላይ በስዕል መፍጠር ማለት ነው፡፡ ንድፍ ማለት በሰው አእምሮ ውስጥ የተፈጠረ ሀሳብ ወደ ተጨባጭነት የሚቀይር ሆኖ ጠጣር በሆኑ መሳሪያዎች እነደ እርሳስ፣ ከሠል፣ ጠመኔ፣ እስክርቢቶ እና በመሳሰሉት በወረቀት ላይ የሚሰራ መሆኑን ግለፅላቸው፡፡

**ልምምድ 1**

መምህር ከዚህ በታች ያለው የፍጥነት ንድፍ ስዕል ተማሪዎች አይተው በእርሳስ ደጋግመው ተለማምደው ከነደፉ በኋላ የነደፉትን ንድፍ ለክፍል እንዲያቀርቡ አበረታቷቸው፡፡ ለየግል ሰርተው ከአቀረቡ በኋላ ተማሪዎች የራሳቸውን ስራ ላይ ብረቱ ን የሚስተካከለውን ሀሳብ እርስ በእርስ እንዲሰጣጡ እና እንዲደናነቁ አድርጉዋቸው፡፡ እንዲሁም በዚህ ስራ ሂደት ውስጥ የአጋጠማቸው ችግር የተረዱትን ነገር እና ችግር ለቀጣይ ስራቸው ደግሞ ምን ማስተካከል እንዳለባቸው እንዲናገሩ አድርጋቸው፡፡ በመጨረሻም ላይደግሞ ተማሪዎችን በማበረታት ማጠቃለያ ሀሳብ ስጡዋቸው፡፡ ለተማሪዎች የሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ የሚቀጥለውን ስራቸውን አሻሽለው እንዲሰሩ ይረዳቸዋል፡፡



**ልምምድ 2**

መምህር ከዚህ በታች የተሰጠውን የእርጋታ ንድፍ ስራ ስዕል ምሳሌ በማድረግ ተማሪዎች አይተው በእርሳስ ተለማምደው ከነደፉ በኋላ የነደፉትን ለክፍል እንዲያቀርቡ አበረታቷቸው፡፡ ከዚህ በኋላ የክፍላችሁ ተማሪዎች የማሻሻያ ሀሳብ ለተማሪው የሰጡትን እርስ በእርሳቸው ያደንቃሉ፡፡ እንዲሁም በዚህ ስራ አካሄዱ ውስጥ ጥንካሬአቸው ምን እንደነበረ በጣም ያስአገራቸው ነገር፣የተገነዘቡትን እና የስራቸውን እጥረት በሚቀጥለው ስራ ውስጥ ማሻሻል ያለባቸው ምን እንደሆነ እንዲናገሩ አድርጓቸው፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎችን በማበረታት ጥንካሬ እና የእየአንዳንዱ ጉድለታቸው ላይ ማጠቃለያ ሀሳብ ስጣቸው፡፡ ለተማሪዎች የሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ የሚቀጥለውን ሀሳብ አሻሽለው እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል፡፡



በዝግታ የተሠራ ንድፍ የሚያሳይ ስዕል

## 1.2 የሜጀር እና የማይነር ቁልፍ

ለዚህ ርዕስ የተሰጠ ክፍለ ግዜ-------------------5

ተማሪዎች ቢየንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ

- የሜጀር እና የማይነር ቁልፍ ለይተው የናገራሉ፡፡
- ሜጀር እስኬል እና ማይነር እስኬል ይሠራሉ፡፡
- የሜጀር እና ማይነር ቁልፍ ትስስር ይገልጻሉ፡፡

### የግንዛቤ 1 ጥያቄ መልስ

መምህር ተማሪዎች የተሰጣቸውን የግንዛቤ ጥያቄ ላይ በቡድን ተወያይተው ለክፍል እነዲየቀርቡ አድርግ፡፡ እሱም ሙዚቃ ሲጫወቱ ወይም ሲያዳምጡ ከፍ ያለውን ድምፅ እና የደስታ ስሜትን የሚፈጥር ወይም ዝግ ያለ ድችጽ እና ስሙን የሚያራራ ስሜት በሰው ውስጥ የሚፈጥር የትኞቹን ቁልፍ ስንጫወት ነው?በማለት ጠይቃችሁ እንዲሳተፉ አድርጉ፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- የቡድን ውይይት፣የየአንዳንድ፣በክፍል ውይይት
- በጥያቄ እና መልስ
- በልምምድ

የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች

ይህን ርዕስ ለማስተማር የሚውሉ የትምህርት መርጃ መሳረያዎች

- ስዕሎች
- የሙዚቃ ምልክቶች

### የመምህሩ ድርሻ

- ተማሪዎች በ5ኛ ክፍል የተማሩትን የተለያዩ የሙዚቃ ርዕሶችን እንዲያብራሩ በመጠየቅ ይህንን ርዕስ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች የሜጀር እና ማይነር ቁልፍ እንዲሁም በእስኬል ላይ በጥንድ ጥንድ እና በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡

- በንኡስ ርእስ ስር የተሰጡትን ተግባሮች ተማሪዎች ያላቸውን እውቀት እና ችሎታን በመረዳት ተማሪዎችን ለማበረታት ስለሚረዳ ወደ ማብራሪያ ሳትገቡ በቡድን ወይም በየግላቸው ሃሳባቸውን እንዲገልጹ አድርጉ፡፡

### ተከታታይ የምዘና ዘዴ

- ከመጀመሪያ ጥያቄዎች እና ተግባሮች ውስጥ ጥቂቶቹን ከክፍል ስራ እና ከቤት ስራ እንዲሰሩ አድርግ፡፡
- ለሰሩት ስራ በየግዜው ትክክለኛውን ግብረ መልስ መስጠት አለብን፡፡

ተማሪዎች ቢየንስ ሊጎናጸፏቸው ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ከስመዘገቡ ብቃታቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ ይህም ሁሉን አወቅን ብለው መሻሻልን እነዳያቆሙ እናበርትተው እንዲሰሩ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ የተማሪዎችን ድርጊቶች አንድ በአንድ መዝግቦ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ስራ ቶሎ ከጨረሱ ተጨማሪ ጥያቄ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያመጡትን የክፍል ታማሪዎች ጋር ለመድረስ ተጨማሪ እርዳታ ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶአቸው ተጨማሪ ትምህርት በየ ርዕሱ ላይ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

### የተግባር 2 መልስ

1. እስኬል ማለት ምን ማለት ነው
2. ሜጀር እስኬል እና ማይነር እስኬል እንዴት መለየት እንደሚቻል በቡድን ተወዬበት

እስኬል የተቀናጀ የድምጽ ቅደም ተከተል ነው፡፡ ሜጀር እስኬል ግማሽ እርምጃ (ድምጽ) ያለው 3ኛ እና 4ኛ ፣ 7ኛ እና 8ኛ መካከል ሲሆን ማይነር እስኬል ደግሞ ግማሽ እርምጃ (ድምጽ) ያለው 2ኛ እና 3ኛ፣ 5ኛ እና 6ኛ ድምጾች መካከል ነው፡፡ በተጨማሪም በሚጀምርበት የፒች ድምፅ ያሳያል፡፡
እስኬል የተቀናጀ ድምጽ ሆኖ እንደየ ሀገሩ ባህል የተለያዩ ዓይነቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ የምዕራባውያን እስኬል ዲያጎኒክ እስኬል ሮያቶኒክ እስኬል ተብሎ የሚታወቅና

የተለያየ 7 ፒች ያለው ነው፡፡እርሱም ሙሉ እርምጃ ዝና ግማሽ እርምጃ የያዘ ነው፡፡

### 1.1.2. የሜጀር ቁልፍ

በዚህ ምዕራፍ ትምህርት የተሠጠ ክፍላ ግዜ …………………..3

- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፏቸው የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ

- የሜጀር ቁልፍ ምን እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡
- የሜጀር ቁልፍ እንዴት እንደሚቀናጅ ለይተው ይናገራሉ፡፡
- የሜጀር እና የማይነር ቁልፍ በኪቦርድ ላይ ሰርተው ያሳያሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- ቅድሚያ በማሳየት
- ውይይት፣በቡድን፣በጥንድ እነ ክፍሉን በሙሉ በማወያየት
- በገለጻ
- በጥያቄና መልስ
- በልምምድ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች**

የትምህርት ይዘት ለማስተማር የሚወሉ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች

- ስዕሎች
- የሙዚቃ መልዕክት

**የመምህር ድርሻ**

❖ ተማሪዎች ስለሜጀር እና ማይነር ቁልፍ እንዲገልጹ በማድርግ ርዕሱን ማስጀመር ይቻላል፡፡

❖ ተማሪዎች በሜጀር ቁልፍ ላይ እነዲወያዩ እና የውይይታቸው ውጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡ በመጨረሻም የፒያቦ ቁልፍ በወረቀት ላይ በማዘጋጀት ወይም ደግሞ ፒያኖ ካለ በማሳየት በቂ ማብራሪያ መስጠት አለብህ፡፡

❖ ከዚህ በታች የተቀመጠው የሜጀር ቁልፍ በኪቦርድ እና በእስታፍ ላይ ያሉትን ድምጾች ለማመሳሰል መጀመሪያ የፐያኖ ቁልፍ ስያሜ እና አጨዋወታቸውን አስተምሩ፡፡




የሀገራችን ቅኝት ምስል በማስታወሻ ከሌላው ጋር ማያያዝ



በክሌፍ እና በጣት አቆጣጠር ጋር ያለውን ግንኙነት በወረቀት ላይ በማዘጋጀት አሳይ





በትምህርት ቤትህ ኪቦርድ ካለ ቀላል የያቶኒክ እስኬልን ( CM) ከዚህ በታች በተሠጠው መንገድ እንዲለማመዱ በማድረግ ልዩ ተሰጥኦና ፍላጎት ያላቸውን ልጆች በይበልጥ አመቻችተህላቸው እንዲለማመዱ አድርጉ፡፡




## ተከታታይ የግንዛቤ ምዘና ዘዴ

- ከመጀመሪያ ጥያቄዎች እና ተግባሮች ውስጥ የክፍል ስራ እና የቤት ስራ እንዲሰሩ አድርግ፡፡
- ለሰሩት ስራ በግዜው ትክክለኛውን ግብረ መልስ መስጠት አለብን
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ብቃታቸው ሊያዝላቸውይገባል፡፡ ይህም አወቅን ብለው መሻሻል እንዲያቆሙ እና በርትተው እንዲሰሩ ሊበረታታ ይገባል፡፡ የተማሪዎች ድርጊቶች አንድ በአንድ መዝግቡ፡፡ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ስራ ቶሎ ከጨረሱ ተማሪዎች ጥያቄ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያመጡትን የክፍል ተማሪዎች ገር ለመድረስ ተጨማሪ እርዳታ ይፈልጋሉ፡፡

መምህር ተማሪዎች የኪቦርድን እና የእስታፍን ስዕል አንስቶ ተግባር 3 ስር በመጽሀፍ ውስጥ የሚገኙትን ጥያቄዎች እንዲሰሩ አድርግ፡፡

**ተግባር 3**

1. **ከዚህ በታች የተሰጠውን የሜጀር ቁልፍ ድምጾች የኪቦርድ እና የእስታፍ ስዕል በማንሳት በኪቦርድ ላያ ለመጻፍ በሙዚቃ እስታፍ ላይ ደግሞ በመስራት እንዲየሳዩ አድርግ፡፡**

ሀ. D ,E,F, G, A, B, C, D

ለ. A, B, C, D, E, F, G, A

ሐ. G ,A ,B, C, D, E, F, G

2. **የሙዚቃ እስታፍ ከዚህ በታች ያሉትን የሙዚቃ ቁልፎች በኖታ እስታፍ ላይ እንዲጽፉ አድርግ**

ሀ. E ሜጀር

ለ. E ሜጀር

ሐ. $A^b$ ሜጀር

**የተግባር 3 መልስ**

መልስ 1

1



2



3



መልስ 2

1.



2.



3



### 1.1.3. **የማይነር ቁልፍ**

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሠጠ ክፍለ ግዜ……………..2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፏቸው የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች

- ስለማይነር ቁልፍ ያብራራሉ
- ማይነር ቁልፍ እንዴት እንደሚቀናጅ ለይተው ያውቃሉ

- ማይነር ቁልፍ ሰርተው ያሳያሉ፡፡

**የመማር ማስተማተማር ዘዴ**

- ቅድሚያ በማሳየት
- ውይይት ፡- በቡድን፣በጥንድ እና ክፍሉን በሙሉ በማወያየት
- በገለጻ
- በጥያቄና መልስ
- በልምምድ

**የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች**

የትምህርቱ ይዘት ለማስተማር የሚውሉ የትመህርት መረጃ መማሪያዎች፡-

- ስዕሎች
- የሙዚቃ ምልዕክት

**የመምህር ድርሻ**

- ተማሪዎች ስለ ሜጀር እና ማይነር ቁልፍ እንዲገልጹ በማድረግ ርዕሱን ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች በሜጀር ቁልፍ ላይ እንዲወያዩ እና የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡
- በመጨረሻም የፒያኖን ቁልፍ በወረቀት ላይ በማዘጋጀት ወይም ደግሞ ፒያኖ ካለ በማሳየት በቂ ማብራሪያ መስጠት አለብህ፡፡
- ከዚህ በታች የተቀመጠው የሜጀር ቁልፍ በኪቦርድ እና በእስታፍ ላይ ያለውን ድምጾች በማመሳሰል መጀመሪያ የፒያኖ ቁልፍ ስያሜ እና አጨዋወታቸውን አስተምሩ፡፡



የ G ማይነር ምሳሌ




**ተከታታይ የግንዛቤ ምዘና ዘዴ**

ከመጀመሪያ ጥያቄዎች እና ተግባሮች ውስጥ ጥቂቶቹን ከክፍል ስራ እና ከቤት ስራ እንዲሰሩ አድርጉ፡፡

ለሠሩት ስራ በግዜው ትክክለኛውን ግብረ መልስ መስጠት አለብን፡፡

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ብቃታቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ ይህን አውቀን ብለው መሻሻልን እንዳያቆሙ እና በርትተው እንዲሰሩ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ የተማሪዎችን ድርጊት አንድ በአንድ መዝግቡ፡፡ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ስራ ቶሎ ከጨረሱ ተጨማሪ ጥያቄ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## ተግባር 4

1. ከዚህ በታድ ያሉትን የሚዚቃ ድምጾች መነሻ በማድረግ ማይነር እስኬል ሰርተህ አሳይ፡፡
    - C ማይነር
    - C ማይነር
    - F ማይነር

**የተግባር 4 መልስ**

1



2.



3.



### 1.1.4. ፒችና የቁልፍ ምልክት

#### ሀ. ፒች

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ............3

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች

- የፒችን ፍቺ ይናገራሉ፡፡
- ፒች በሙዚቃ ውስጥ የለውን ጥቅም ለይተው ይገልጻሉ፡፡

**የመማር ማስተማር ዘዴዎች**

- ቀድሞ በማሳየት
- ውይይት በቡድን፣በጥንድ እና በክፍል
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ
- ልምምድ

**የትምህርት መርጃ መሳሪያ**

**ለዚህ ትምህርት ይዘት የሚውል የትምህርተ መርጃ መሳሪያዎች**

- ስዕሎች
- የሙዚቃ ምልክት

**የመምህሩ ድርሻ**

- ተማሪዎች ስለማይነር ቁልፍ እንዲያብራሩ በመጠየቅ የትምህርቱን ርዕስ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ስለ ፒች በጥንድና በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ የውይይታቸውን ውጤት ለክፍላቸው እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡
- በንኡስ ርዕስ ስር የተሰጠውን ተግባር የተማሪዎችን እውቀት እና ችሎታ በመረዳት ተማሪዎችን ለማበረታት ስለሚረዳ ወደ ገለጻ ሳትገቡ በቡድን ተወያይተው ሀሳባቸውን እንዲያቀረቡ አድርጉ፡፡

## ተከታታይ የግንዛቤ መመዘኛ ዘዴዎች

- ከመጀመሪያ ጥያቄና ተግባር ውስጥ ጥቂቶቹን የክፍል ስራና የቤት ስራ እንዲሰሩ አድርግ
- ለሰሩት ስራ በጊዜው ትክክለኛውን ግብረ መልስ መስጠት አለብህ
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ብቃታቸው እንዲመዘገብላቸው ይገባል፡፡
- ይህም አወቅን ብለው ማሻሻልን እንዳያቆሙ እና በርትተው እነዲሰሩ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ የተማሪዎችን ድርጊት አንድ በአንድ መመዝገብ አለበት፡፡ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚሰራውን ስራ ቶሎ ከጨረሱ ተጨማሪ ጥያቄ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎነጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያመጡትን የክፍል ተማሪዎች ጋር ለማድረስ ተጨማሪ እርዳታ ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶአቸው ተጨማሪ ትምህርት በርዕሱ ላይ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

የግንዛቤ ጥያቄ 2 መልስ

ሀ. በሙዚቃ ውስጥ የፒች ጥቅም ምንድን ነው? የሚለውን ጥያቄ እንድመልሱ ያድረጉ

መልስ፡ ሙዚቃ ስንጨወት የሙዚቃውን መነሻ የሚያሳን ነው፡፡

## 1.1.5. የቁልፍ ምልክት

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ግዜ -----------3

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎነጹፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡

- የቁልፍ ምልክት ያብራራሉ
- የቁልፍ ምልክት ለይተው ያሳያሉ

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ቀድሞ በማሳየት
- ውይይት በቡድን፣በጥንድ እና በክፍል
- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ
- ልምምድ

### የትምህርት መርጃ መሳሪያ

### ለዚህ ትምህርት ይዘት የሚውሉ የትምህርተ መርጃ መሳሪያዎች

- ስዕሎች
- የሙዚቃ ምልክት

### የመምህሩ ድርሻ

- ተማሪዎች ስለ ፒች እንዲያብራሩ በማድረግ የትምህርቱን ርዕስ ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች በቁልፍ ምልክት ትርጉም ላይ በጥንድ እና በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ ለክፍሉ እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡
- በንዑስ ርዕስ ስር የተሰጠውን ተግባር የተማሪዎችን እውቀት እና ችሎታን በመረዳት ተማሪዎችን ማበረታታት ስለሚረዳቸው ወደ ገለጻ ሳትገቡ በቡድን ተወያይተው እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡

- የሁሉም እስኬል ቁልፎች ካስፈለገ ቀድሞ በማዘጋጀት አመቺ ሁኔታ ካለ ቁልፎቹን እንደ ፔሬዲክ ቴብል በግድግዳ ላይ በማንሳት ተማሪዎች ከላዩ ለይ እንዲማሩ ማድረግ፡፡




## ተከታታይ የግንዛቤ ምዘና ዘዴ

- ከመጀመሪያ ጥያቄ እና ተግባሮች ውስጥ ጥቂቶቹን እንደ ክፍል ስራና የቤት ስራ እንዲሰሩ ማድረግ ይቻላል፡፡
- ለሰሩት ስራ በጊዜው ትክክለኛውን ግብረ መልስ መስጠት አለበት፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ብቃታቸው እንዲመዘገብላቸው ይገባል፡፡
- ይህም አወቅን ብለው ማሻሻልን እንዳያቆሙ እና በርትተው እነዲሰሩ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ የተማሪዎችን ድርጊት አንድ በአንድ መመዝገብ አለበት፡፡ በተጨማሪም በክፍል ውስጥ የሚሰራውን ስራ ቶሎ ከጨረሱ ተጨማሪ ጥያቄ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያመጡትን የክፍል ተማሪዎች ጋር ለማድረስ ተጨማሪ እርዳታ ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶአቸው ተጨማሪ ትምህርት በርዕሱ ላይ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

**የተግባር አምስት መልስ**

የትኛው ቁልፍ፣ሻርፕ፣ፍላት ወይም ናቹራል መሆናቸውን ለይተን የምናውቅበት ነው፡፡

- የሙዚቃ የቁልፍ ምልክት ድምጽ  የትኛው በመስመር ላይ እና በባዶ ቦታ በሙዚቃ እስታፍ ላይ እንደሚገኝ ለይተው የሚያሳዩ ናቸው፡፡

## 1.3 ስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልም

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሠጠ ክፍለ ግዜ……………..7

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፏቸው የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች ፡-

- ስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልም ለይተው ያውቃሉ፡፡
- የስነ-ትያትር እና ፊልምን ተውኔት ስነ-ጽሁፍ ይጽፋሉ፡፡
- ትያትር ያዘጋጃሉ፡፡

### የርዕሱ አብይ ነጥቦች

- ስነ-ትያትር
- ተውኔት
- የተውኔት ስነ-ጽሁፍ መጻፍ
- ዝግጅት
- ስነ-ፊልም

### የትምህርት ይዘት መግለጫ

የትያትር ትርጉም መነሻ የግሪክ ቃል ሲሆን "Theatron" ከሚለው ቃል የመጣ ነው፡፡ "Theatron" ማለት አንድን ነገር የማናይበት ቦታ ወይም የምናይበት ቦታ ነው፡፡ ቲያትር በየ እለት ኑሮአችን ውስጥ የምናከናውነውን ድርጊት የሚያሳይ ነው፡፡ በትያትር ውስጥ የሚታየው ድርጊት እና የማናየው ድርጊት ድራማ ይባላል፡፡

ድራማ ስራ ወይም በድርጊት በማሳየት መስራት ማለት ነው፡፡ ድራማ የሚለው ከግሪክ ቃል"dran" ከሚለው የመጣ ነው፡፡ ትርጉሙ መስራት እነ በተግባር ማሳየት ነው፡፡ ድራማ በድርጊት ከማሳየት በፊት በድርሰት መልክ በጽሁፍ የሚዘጋህ ሆነ በመቀጠል የትያትር ባለሙያዎች በመድረክ ላይ ተመልካች ባለበት ቦታ እና አስፈላጊው ቁሳቁስ በተሟላበት ቦታ በቀትታ ከመድረክ ላይ ለተመልካቾች ሲያቀርቡ ትያትር ሆነ ማለት ነው፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴዎች

- ውይይት በቡድን፣በጥንድ
- በማሳየት

- ገለጻ
- ጥያቄና መልስ
- የፕሮጀክት ዘዴ
- ልምምድ

## የትምህርት መረጃ መሣሪያ

- የመለማመጃ ክፍል
- የምስል ድምጽ ማጫወቻ

### የመምህሩ ድርሻ

- የተሰጠውን ተግባር ከማበረታት በፊት ተማሪዎች ባለፈው ትምህርቱ ላይ ያላቸውን ልምድና ግንዛቤ እንዲለዋወጡ አድርጉ፡፡
- ተማሪዎች በቡድን በመሆን የትያትር ተውኔት ፣የተውኔት ጽሁፍ መጽሀፍ፣ ዝግጅት እና በፊልም ላይ ያላቸውን ሀሳብ እንዲለዋወጡ ማድረግ
- የተሰጠውን ተግባሮች እና በግል፣በጥንድ፣በቡድን፣ በክፍል፣በቤት ስራ እና በፕሮጀክትእንዲሰሩ ምራቸው፡፡
- የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎነጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ካስመዘገቡ የቲቶሪያን ፕሮግራም በማዘጋጀት እርዳቸው፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎነጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ መበረታታት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ሁሉን አወቅን ብለው መሻሻልን እነዳያቆሚና በርትተው እንዲሰሩ ሊበረታቱ ይገባል፡፡

## የተግባር 5 መልስ

1. ድራማ ማለት በስራ ወይም በተግባረ ማሳየት ማለት ነው፡፡ ድራማ በተግባር ከማሳየት በፊት በጽሑፍ መልክ የሚዘጋጅ ሲሆን ትያትር በመድረክ ላይ የትያትር መሳሪያዎችን በሚያስፈልግበት መንገድ አዘጋጅቶ ለተመልካች በቀጥታ ማሳየት ነው፡፡
2. ተውኔቱ በአንድ ትያትር ውስጥ ሰዎች ገጸ ባህርያትን ወክለው በመድረክ ላይ ቀርበው በትእይንት የሚያሳዩት ጽሁፍ ነው፡፡

## የተግባር 6 መልስ

1. የስነ ተውኔት ችሎታ የሚገኘው በተፈጥሮ ሆኖ ተዋንያን ችሎታቸውን በትምህርት፣በስልጠና፣በልምድ በይበልጥ እያሻሻሉ ያሳድጋሉ፡፡

## የተግባር 7 መልስ

1. የተውኔት ጽሁፍ ልብ ወለድ አካል ሆኖ ለትእይንት የተዘጋጀ ጽሁፍ ነው፡፡ የተውኔት ጽሁፍ ለትዕይንት በቃለ ተውኔት በመቀባበል ላይ ተመስርቶ ተዋኒያን እና ተውኔት የሰውነት እንቅስቃሴን አቀናጅቶ የሚታይ ነው፡፡
2. የተውኔት ጽሑፍ ለመጻፍ የሚረዱን ዘዴዎች ከዚህ በታች የተጠቀሱ ናቸው፡፡
   - ፍሬ ሀሳብ
   - ሀሳብን ማብራራት
   - መጫወት
   - አካባቢን መቃኘት
   - ጥያቄና መልስ ከሰዎች ጋር ማድረግ

## የተግባር 8 መልስ

1. የስነ-ፊልም እና የስነ-ትያትር ልዩነት፡- ፊልም ካሜራን በጠቀም የማያስፈልገውን ቦታ ከውስጥ ቆርጦ በመውሰድ ፣በመገምገም፣የሚዘጋጅ ነው፡፡ትያትር ግን በመድረክ

ላይ በቀጥታ ተመልካቾች ባሉበት ቦታ ይቀርባል፡፡ በፊልም ውስጥ ተመልካቾች በቀጥታ ማግኘት ግዴታ አይደለም፡፡ ተመልካቾችን በእስክሪን ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ማየት ይቻላል፡፡ ትያትር ደግሞ በመድረክ ላይ ስለሚመሰረት ተመልካቾችም በቀጥታ መከታተል አለባቸው፡፡

2. ፊልም ለመስራት የሚረዱን መሳሪያዎች እንደ ካሜረ፣የምስል ድምጽ መቅጃ መብራት፣የድምጽ መቅጃ ፣ኮምፒውተር፣ካሜራ ተሸካሚና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ተከታታይ ግንዛቤ መመዘኛ ዘዴዎች

ውይይት በቡድን እና በጥንድ

- ጥያቄ እና መልስ
- በቡድን እና በግል ማሳየት
- በግል ገለጻ
- በቡድን ገለጻ
- የቤት ስራ
- በሙከራ
- ፈተና ስም
- መጥሪያ

**የምዕራፍ 1 መልመጃ መልስ**

I.

1.እውነት 2. ሐሰት 3. ሐሰት 4. እውነት 5. እውነት 6. ሐሰት 7. ሐሰት 8. ሐሰት 9. ሐሰት 10. እውነት 11. እውነት

II.

1. D 2. B 3. A 4. D 5. D 6. D 7. A 8. D 9. B 10. A 11. A 12. D 13. A
14. D 15. D

III.መልስ

1. አስኬል
2. 3ኛ እና 4ኛ-7ኛ እና 8ኛ

3. E ማይነር



4.



5.



6.

# ምዕራፍ 2: የፈጠራ ስራ ችሎታ

ለዚህ ርዕስ የተሠጠው ክፍለ ግዜ…………28

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ፡-

- የትሬብል ክሌፍ እና የቤዝ ክሌፍ ልዩነት ለይተው ያውቃሉ
- ቀላል ዜማ ያለውን ምት ይለምዳሉ፡፡
- የከፍ ያለ ድምጽ እና ዝግ ያለ ድምጽ ለይተው ያስተውላሉ
- ንድፍ እና ስነ-ስዕል መካከል ያለውን ትስስር ያስተውላሉ፡፤

የቀለም ቅብ በንድፍ እንዴት እንደሚነደፍ ይለማመዳሉ፡፡

ቀለል ያሉ የቀለም ቅብ ስራን ይነድፋሉ፡፡

የግል ሀሳባቸውን በስነ-ትያትር እና በስነ-ፊልም በመጠቀም መገለጽ እንዳለባቸው ያውቃሉ፡፡

**መግቢያ**

በምዕራፍ አንድ ውስጥ የሜጀር እና የማይነር እንዲሁም የፒች የቁልፍ ምልክት ጥቀሙ ምን እንደሆነ ተምራችኋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ደግሞ ከፍ ያለ ድምጽ እና ዝቅ ያለ ድምጽ  ትሬብል ክሌፍ እና ቤዝ ክሌፍ ላይ ቀለል ያሉ ዜማዎችን እንዴት ከሙዚቃ እስታፍ ላይ ግዜም እንዳለባቸው ይማራሉ፡፡ እንዲሁም ንድፍ መነሻ እና የስነ-ስዕል ዓይነት እንደሆነ ይማራሉ፡፡ አንድን ስዕል ለመስራት በቅድሚያ የስዕሉን ስራ በአጠቃላይ በንድፍ ማሳየት፡፡ ስለዚህ ንድፍ በማንኛውም የስዕል ስራ እና ስዕል መካከል ጥልቅ ትስስር አላቸው፡፡ ማንኛውም የስዕል ስራ እና ስዕል ሁሉ በሚሰራበት ስራ ስልትና ዘዴ ላይ ተመርኩዞ ልዩነት አለው፡፡ ንድፍ በእየ አንዳንዱ ሲነደፍ በምን አይነት መንገድ እና ዘዴ በስራው ላይ ልዩነት አለው፡፡

የውስጥ ሀሳባችንን በምንገልጽበት መንገድ ውስጥ አንዱ ስነ-ትያትር ነው፡፡ ሀሳባችንን በትያትር መግለጽ ስንል አንድ ሰው በአእምሮ ውስጥ ብዙና የተአይት ሃሳብ ያለው ከሆነ የንን ሀሳብ ወደ ፈጠራ በመቀየር በትያትር መቀየር ይቻላል፡፡ ተማሪዎችም ሀሳባቸውን ወይም መገለጽ የሚፈልጉትን ነገር ትያትር በመጠቀም መግለጽ ይችላሉ፡፡

**የምዕራፉ ዋና ዋና ይዘቶች**

2.1. ትሬብል ክሌፍ እና ቤዝ ክሌፎች ላይ በዜማ ቀላል ምት ከፍ ያለ ድምጽ እና ዝቅ ያለ ድምጽ ያላቸው፡፡ክፍለ ግዜ 5

2.2. ለማቅለምና ለማተም መንድፍ (የውሃ ቀለም) ክፍለ ግዜ 12

2.3. የቲያትር፣የምስለ ድምጽ እና የፎቶ ሀሳብ መገለጫ ክፍለ ግዜ 8

2.4. የውዝዋዜ አላባውያን ክፍለ ግዜ 3

## 2.1 ቀለል ያሉ ዜማዎችን በክሌፎች ላይ መፃፍ

የግንዛቤ ጥያቄ 1

የቀጭን ድምጽ መነሻ ፣ የወፍራም እና የመካከለኛ ድምጽ ለይተው ለመስማት ወይም ለመዘመር የምንጠቀምባቸው ምልክቶች ምን ምን ናቸው? በማለት ጥያቄ በመጠየቅ ማስጀመር፡፡

መምህር/ርት፡ ለተማሪዎች የተሰጠውን የመመዘኛ ጥያቄ እንዲወያዩበት እና እርስ በእርስ ገለጻ እንዲሰጡበት በማድረግ በተጨማሪም በቂ ገለጻ ስጥ፡፡

**ሀ. በትሬብል ክሌፍ እና በቤዝ ላይ ቀለል ያሉ ዜማዎችን ይለማመዳሉ፡፡**

ለዚህ ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ግዜ ..........3

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡

- ትሬብል ክሌፍ እና ቤዝ ክሌፍ የላቸውን ልዩነት ይገልጻሉ፡፡
- ቀለል ያሉ ምት ያላቸውን ዜማ ይጫወታሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

- ቅድሚያ በማሳየት
- ውይይት በቡድን፣በጥንድ እና በክፍል
- በገለጻ
- በጥያቄ እና መልስ
- በልምምድ

## የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች

ይህን ርዕስ በማስተማር የሚውሉ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች

- የቁልፍ ምልዕክቶች እና የሙዚቃ እስታፍ በትልቅ ወረቀት ላይ በማዘጋጀት

## የመምህሩ ድርሻ

- ተማሪዎችን ስለ ቁልፍ ምልዕክት እነዲናገሩ በመጠየቅ ርዕሱን ማስጀመር ትችላላችሁ
- ተማሪዎችን ትሬብል ክሌፍ እና ቤዝ ክሌፍ ቀለል ባለ ዜማ በጥንድ እና በቡድን እንዲወያዩ አድርገህ ለክፍል ተማሪዎች እንዲቀርቡ አድርግ

❖ በዚህ ትምህርት ርዕስ ውስጥ የተሰጡትን ድርጊቶች ላይ በመመርኮዝ ተማሪዎቹ በፊት ያላቸውን ችሎታ እና እውቀት በመረዳት ተማሪዎችን ለማበረታት ገለጻ ከመስጠት በፊት በቡድን ተወያይተው ሀሳብ እንዲሰጡ አድርግ፡፡

## ተከታታይ የምዘና ጥያቄዎች

- ድርጊቶችን እና የመጀመሪያ ጥያቄዎች ላይ በመመርኮዝ የክፍል ስራ እና የቤት ስራ እንዲሰሩ አድርግ
- ለሰሩት ስራ በግዜው ትክክለኛውን ግብረ መልስ መስጠት አለብን፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ብቃታቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ አወቅን ብለው መሻሻልን እንዳያቆሙ እና በርትተው እንዲሰሩ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ የተማሪዎች ድርጊት አንድ በአንድ ሊመዘገብ ይገባል፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ካመጡ የክፍል ተማሪዎች ጋር በማድረስ ተጨማሪ እርዳታ ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ የተለየ ትኩረት ተሰጥቷአቸው ተጨማሪ ትምህርት በየርዕስ ላይ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## የተግባር 1 መልስ

በሙዚቃ እስታፍ ላይ ክሌፎችን መጠቀም ለምን አስፈለገ? በማለት አሰራ:: በመጨረሻም መልሱን ከዚህ በታች በተሠጠው መሰረት መልስ፡፡ ከተሰጠህ ድምጽ ውስጥ ሳትወጣ ቀጭን ድምጽ፣ወፍራም ድምጽ ፣መካከለኛ ድምጽ ለይተህ በማውጣት በመመሪያው መሰረት እርዳቸው፡፡

**ለ. ከፍ ያለ እና ዝግ ያለ ድምጽ**

**ለዚህ ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ…………………2**

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች

- ከፍ ያለ እና ዝግ ያለ ድምጽ ለይተው ያውቃሉ
- ከፍ ያለ እና ዝግ ያለ ድምጽ በሙዚቃ ውስጥ ያለውን ጥቅም ይገልጻሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

- ቅድሚያ በማሳየት
- ውይይት በቡድን፣በጥንድ እና በክፍል
- በገለጻ
- በጥያቄ እና መልስ
- በልምምድ

## የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች

ይህን ርዕስ ለማስተማር የሚውሉ የትምህርት መረጃ መሳሪያዎች

- የሙዚቃ እስታፍ እና ክሌፎችን በወረቀት ወይም በካርቶን ላይ በትልቁ አስምሮ ማዘጋጀት






## የመምህሩ ድርሻ

- ተማሪዎች ቤዝ ክሌፍ እና ትሬብል ክሌፍ ቀላል ባለ ዘዴ እንዴት መጫወት እንደሚቻል በመጠየቅ ርዕሱን ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ከፍ እና ዝቅ ባለ ድምጽ ላይ በቡድን እና በጥንድ እንዲወያዩ በማድረግ ለክፍል ተማሪዎች እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡
- በዚህ ትምህትት ርዕስ ውስጥ የተሰጡትን ንኡስ ርዕስ ላይ ተማሪዎች ያላቸውን እውቀት እና ግንዛቤ በመረዳት ተማሪዎችን በማበረታት ገለጻ ከመስጠት በፊት በቡድን ተወያይተው ሀሳብ እንዲሰጡ አድርጉ፡፡

  ተከታታይ የምዘና ጥያቄዎች

  ድርጊቶች እና የመጀመሪያ ጥያቄዎች ላይ በመመርኮዝ የክፍል ስራ እና የቤት ስራ እንዲሰሩ አድርጉ፡፡

  ለሠሩት ስራ በጊዜው ትክክለኛውን ግብረ መልስ መስጠት አለብን፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉት ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ብቃታቸው ሊያዝላቸው ይገባል፡፡ አወቅን ብለው መሻሻልን እንዳያቆሙ እና በርትተው እንዲሰሩ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ የተማሪዎች ድርጊት አንድ በአንድ ሊመዘገብ ይገባል፡፡

- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎነጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያመጡትን የክፍል ተማሪዎች ጋር ለማድረስ ተጨማሪ እርዳታ ይፈልጋሉ፡፡ ስለዚህ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶአቸው ተጨማሪ ትምህርት በየርዕሱ ላይ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** መምህር/ርት ድርጊት 2፣ 3 እና 4 ስር የተጻፉትን ሙዚቃ ተማሪዎች በመደጋገም እንዲለማመዱ ማድረግ፡-

- ተማሪዎች እንዲለማመዱ በቅድሚያ አሳያቸው
- በሙዚቃ አስታፍ ላይ መጻፍ እና ማዜም እንዲቸሉ ሁኔታ አመቻቹላቸው፡፡

## የተግባር 2 መልስ

ከዚህ በፊት የነበረውን የልምምድ መዝሙር በሙዚቃ እስታፍ ላይ እና ፒያኖ በማነጻጸር ደጋግመው ይለማመዱ፡፡

**ማሳሰቢያ፡-** ጥቁር ቀለም ያላቸው ቁልፎች በድምጽ እንዲለማመዱ ከታዘዙ ብቻ ማሳየት እንደሆነ አስታዉቃቸው (ንገሯቸው)








# የተግባር 3 መልስ

**ከዚህ በታች የተጻፈውን ሙዚቃ ከፍ ባለ ድምፅ (በቀጭን ድምፅ) በትንሹ ኪቦርድ ላይ እንድለማመዱ ያሰዩዋቸው፡፡**




## የተግባር 4 መልስ

1. ከዚህ በታችን ያሉትን በዝግታ (ወፍራም) ድምጽ እንዲለማመዱ አድርጉ፡፡



2. ቸጥሎ የተሰጠውን ዜማ ከመምህራችሁ ጋር ተለማመዱ፡፡



C E G C G E C E G C G E C



C D E C C D E C C C E E G G C C C



3. ከዚህ በታች በሙዚቃ እስታፍ ላይ የተፃፉትን ሙዚቃዎች ተራ በተራ እንድለማመዱ ያድረጉ፡፡



4. ከዚህ በታች በሙዚቃ እስታፍ ላይ የተጻፉትን ሙዚቃ ተራ በተራ እንዲለማመዱ አድርጋቸው፡፡



5.



ማሳሰቢያ፡- **መምህርት/ር** ድርጊት 2፣3፣እና 4 ተጽፈው ያሉትን ሙዚቃ ተማሪዎች
በመደጋገም እንዲለማመዱ አድርግ
ተማሪዎች እንዲለማመዱ በቅድሚያ አሳዩ
በሙዚቃ እስታፍ ላይ መጻፍና ማዜምን ለይተው እንዲያውቁ ሁኔታውን አመቻቹላቸው፡፡

## 2.2 የቀለም ቅብ እና የህትመት ንድፍ

ለዚህ ርእስ የተሰጠው ክፍለ ግዜ ……….12

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ፡-

- የቀለም ቅብ እና የሕትመት ስራ ለይተው ያውቃሉ፡፡
- ቀለል ባ ነገሮች ላይ የቀለም ቅብ ንድፍ ይነድፋሉ፡፡
- የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም የቀለም ቅብ ንድፍን ይሰራሉ፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

- በምልከታ
- በማሳየት
- ልምምድ
- ውይይት በቡድን፣በጥንድ እና በክፍል
- ገለጻ
- በጥያቄ እና መልስ
- በፕሮጀክት መልክ

የትምህርት መርጃ መሳሪያ

ይህን ርዕስ ለማስተማር የሚውሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- የሚለማመዱበት ክፍል /እስትድዮ/
- ቻርት
- ፖስተር

### የመምህር ድርሻ

### ተማሪዎች በንድፍ ስራ ላይ ባላቸው ሀሳብ ላይ በመነሳት ርዕሱን ማስጀመር

ተማሪዎች በንድፍ እና በስዕል መካከል ያለውን ትስስር በቡድናቸው እንደሚወያዩ ማድረግ የተወያዩትን ለክፍል እንዲያቀርቡ ማድረግ፡፡

- በዚህ ትምህርት ርዕስ ውስጥ የተሰጡትን ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች ያላቸውን እውቀት እና ግንዛቤ በመረዳት ተማሪዎችን ለማበረታታት ገለጻ ከመስጠት በፊት በቡድን ተወያይተው ሀሳብ እንዲሰጡ እድርጉ፡፡

- የተሰጠውን ተግባር እና ጥያቄ ውስጥ ጥቂቶቹን ወስደህ የክፍል ስራ እና የቤት ስራ እንዲሰሩ አድርጉ፡፡
- በሰሩት ስራ በጊዜው ትክክለኛውን ግብረ መልስ መስጠት አለብን፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ እንዲሁም ብቃታቸው ሊመዘገብላቸው ይገባል፡፡ በደንብ ተገነዘብን ብለው እንዳይዘናጉ መከታተል እና ማበረታት ይገባል፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያመጡትን የክፍል ተማሪዎች ጋር ለማድረስ ተጨማሪ እረዳታ ይፈልጋሉ፡፡ የተለየ ትኩረት ለመስተት ተጨማሪ ትምህርት ሊሰጣቸው የገባል፡፡
- የተማሪው የእየአንዳንዱ ስራ ካልተመዘገበ ተማሪው ዋጋ እንደሌለው አውቆ ሊሰላቹ እና ሊዘናጉ ስለሚችሉ ስራቸው ሊመዘገብ የገባል፡፡

## የተከታታይ የምዘና ጥያቄ

- የቡድን እና የግል ጽብረቃ
- ዘገባ (ገለጻ)
- የአፍ ጥያቄ
- ሙከራ
- ፈተና
- ፕሮጀክት በቡድን እና በግል

## የድርጊት አምስት መልስ

መምህር /ት የንድፍ ትርጉም ላይ ተማሪዎች በግል በግል በቂ ግዜ እንዲያስቡበት በማድረግ ከዚያም ትርጊም እና የስራውን ምንነት ከእንደዚህ በታች አስመገዝግቧቸው፡፡ ንድፍ የአንድ ነገር መነሻ ወይም የአንድ የስነ-ስዕል መነሻ መሆኑን ፣ አንድ ሰው ንድፍን ሲነድፍ በትክክል ካልሰራ የቀለምቅብ፣ቅርጻ ቅርጽ፣የህትመት ስራን በደንብ መስራት እንደማይቻል ባለፈው ምእራፍ ላይ እንደተማሩ አስታውሷቸው፡፡ መስመሮች በተቀራረበ እና በማራራቅ ሲሰሩ ወይም ደግሞ በስመሮችን በማሳከር ብርሃን እና ጥላን እንዲፈጥሩ አስገንዝብ፡፡ አንድ መስመር ከሌላኛው መስመር ሲቀራረብ (ሲጠጋ) ጣለ፣ጨለማ እና ውፍረትን የሚፈጥር ሲሆን፣መስመሮች ሲራራቁ ደግሞ ብርሃን እና መሳሳትን የሚያሳይ መሆኑ ረስህ/ሽ በእርሳስ መስመሮችን በመጠቀም አሳይ፤፤

የምናሰምረው መስመር ወፍራም (ጥቁር)የሚሆነው እርሳሳችንን ስንጫነው መሆኑን በተግባር አሳያቸው፡፡

በንድፍ ውስጥ መስመር ሲሰመር የሚጠቁው (የሚወፍረው) ምን ሲሆን እነደሆነ ከዚህ በታች በተዘረዘረው አስመዝግባቸው፡፡የሚሰራው ነገር ጨለማ ወይም ጥላ ውስጥ ከሆነ በተቀራኒው የብርሃን ምንጭ መኖሩ እንደሆነ እና እንዲሁም ጠንካራና ትልቅ ክብደት ያለው እይታ እንዳለው አስረዳ፡፡ የምናሰምረው መስመር ቀጭን ወይም ስስ መሆን የሚችለው ንድፍ የምንነድፍበት እርሳስ በደንብ ሳንጫነው እነደሆነ ሰርተህ አሳይ፡፡ በንድፍ ስራ ውስጥ የሚሰመረው መስመር ቀጭን (ስስ) ከሆነ የሚገልጸው ከዚህ በታች የተሰጠውን ገለጻ በደንብ አስገንዝናቸው፡፡ የሚሰራው ንድፍ ብርሃን የሚገልጽ ወይም በብርሃን አቅጣጫ ከሆነ ብርሃን እንዳለ እና ትልቅ ክብደት የሌለው እይታ እንደሆነ አስመዝግባቸው፡፡ ሰለዚህ ንድፍ የሚነደፍበት መንገድ እና ዘዴ በመስመር ላይ ይመሰረታል፡፡ የቀለም ቅብ፣ቅርጻ ቅርጽ እና ህትመት ብለን የምንለያቸው በጥልቀት እንዲገነዘቡ አድርግ፡፡ የሚነደፍ ንድፍ በሚሰራው ስነ ስዕል የየራስ የሆነ ዘዴ እና ልዩነት አለው ማለት ነው፡፡

## ልምምድ 1

የውሃ ቀለም ንድፍ ስራ ከዚህ በታች በተለያዩ እርሳሶች እየተጠቀሙ በግል በግል ሆነው እንዲለማመዱ አድርግ፡፡

የውሃ ቀለም የሚገኝ ከሆነ የውሃ ቀለም እየቀቡ ይለማመዱ፡፡ ከጨረሱ በኋላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡ የማሻሻያ ሀሳብ ከተለዋወጡ በኋላ በየአንዳንዱ ስራቸው እንዲደናነቁ አድርግ፡፡እንዲሁም በሰሩት ስራ ላይ ጠንካራ ጎናቸው ምን እንደሆነ፣በጣም ያስቸገራቸው ስራ ደግሞ ምን እንደሆነ፣ምን እንደተገነዘቡ እና በሚቀጥለው ስራቸው ምን ማሻሻል እንዳለባቸው እንዲናገሩ አድርግ፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎችን በማበረታታት ጠንካራ ስራቸውና ማሻሻል ያለባቸው ላይ ማጠቃለያ ሀሳብ ይሰጣቸው፡፡ የሚሰጣቸው ማጠቀለያ ሀሳብ የሚቀጥለውን ስራ አሻሽለው እንዲመጡ ያግዛቸዋል፡፡ ነገር ግን ተማሪዎች በቅድሚያ የሰሩት የውሃ ቀለም ንድፍ ስራ መንገድ እና ዘዴ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ወሳኝ ስለሆኑ በደንብ አስገንዝባቸው፡፡ የቀለም ቅብ ፎርም እና የሚሰራበት ቀለም ላይ በጣም በትኩረት የሚሰራ ነው፡፡ የቀለም ቅብ ውስጥ የሚነደፈው ንድፍ የሚጠቀሙትን የቀለም ዓይነት ላይ በመመስረት ልዩነት ሊኖረው እንደሚችል በደንብ በመረዳት

ለተማሪዎቹ አስረዳ፡፡ በሚበጠበጥ የውሃ ቀለም የሚሰራ ከሆነ ተማሪዎቹ የሚነድፉት ንድፍ በቀጭን እና ስስ መስመር መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም መስመሩ ወፍራም (ጥቁር) ሆኖ ከተሰመረ ቀለሙ የውሃ ቀለም ከሆነ በመጀመሪያ ተማሪዎች በእርሳስ የነደፉት ንድፍ ከቀለሙ ስር ወጥቶ ይታያል፡፡ ወይም ይበላሻል ማለት ነው፡፡ ስለዚህ መስመሩ በስስ መስመር  መሰመር ግዳጅ እንደሆነ በደንብ ማስረዳት፡፡

በዘይት የሚቀጥን ቀለም የሚሰራ ከሆነ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ተቃራኒ በወፍራም እና በጥቁር መስመር መጠቀም አለባቸው፡፡ ምክንያቱም በስስ መስመር የሚሰራ የዘይት ቀለም ንድፍ በቀላሉ ቀለም ሲቀባ ሊጠፋ ይችላል፡፡ ስለዚህ የዘይት ቀለም ስራ ንድፍም በወፍራም (ጥቁር) መስመር መጠቀም እንዳለባቸው በጥልቀት ማስገንዘብ ይኖርብናል፡፡ ተማሪዎች ወደ ልምምድ ከመግባታቸው በፊት የስራው ሂደት እና የሚጠቀሙበት የቀለም አይነት ለይተው ማወቅ እንደለባቸው ከነገርናቸው በኋላ ተማሪዎች የሚሰራውን ስራ መረዳት እና አለመረዳታቸውን ለመለየት አካሁዱን እነ የስራውን ባህሪ ከዚህ መላይ በተሰጠው መግለጫ መሰረት አንዳንድ ጥያቄዎችን መጠየቅ፡፡



## ልምምድ 1

መምህር/ት ከዚህ በታች የተሰጠውን ስራ በተሰጠው ቅደም ተከተል መሠረት ተማሪዎች ድርጊቱን እንዲሰሩ አድርግ፡፡

1. በወረቀት ላይ ቀላል የሆነ የንድፍ ፎርም እንዲሰሩ አድርግ፡፡
2. የተማሪዎችን ንድፍ ተመልክተህ መሻሻል ያለባቸውን እንዲያሻሽሉ አስተያየት ስጣቸው፡፡ በአካባቢያቸው የሚያገኙትን ቀለም እንዲቀቡ አድርግ፡፡
3. ማሻሻል (ማስተካከል) ያለባቸውን ነገር ካስተካከሉ በኋላ ለክፍል ተማሪ አቅርቡ፡፡

መምህር/ት ተማሪዎች ስራቸውን ወደ ፊት ለፊት ወጥተው እንዲያሳዩ አድርግ፡፡ በመቀጠል በስራቸው ላይ ጠንካራ እና ደካማ ጎናቸውን በመነጋገር እርስ በእርስ እንዲደናነቁ አመቻችላቸው፡፡ በመቀጠል እንዲሁም በሰሩት ስራ ውስጥ ጠንካራ ጎናቸው ምን እንደሆነና በጣም ያስቸገራቸው ነገር ደግሞ ምን እነደሆነ፣የተገነዘቡትንና ድክመታቸውን በሚቀጥለው ስራቸው ውስጥ ምን ማሻሻል እንደለባቸው በግልበግል እንዲነጋገሩ አድርግ፡፡ በመጨረሻም የማጠቃለያ ግብረ መልስ ስጣቸው፡፡

## ልምምድ 2

ከዚህ በታች የተቀመጡትን የቅርጻ ቅርጽ ንድፍ ስራ ስዕል በተራ በተራ በእርሳስ እንዲነድፉ አድርግ፡፡ ከዚህ በፊት ንድፍ እንዴት በምን አይነት መንገድ የቅርጻ ቅርጽ ንድፍ ስራ እንዴት እንደሚሰሩ ከዚህ በታች በተሰጠው ገለጻ በደንብ አስገንዝባቸው፡፡ የቀለም ቅብ ስራ ንድፍና የቅርጻ ቅርጽ ስራ ንድፍ ልዩነት እንዳለው አስገንዝባቸው፡፡ የቅርጻ ቅርጽ ስራ ንድፍ የሚሰራበት መስመር ፎርም የቀለም ቀብ ስራ ንድፍ ከሚሰራበት መስመር የደመቀ እና ጥቁር እንደሆነ ማወቀወ አለባቸው፡፡ እንዲሁም የቅርጻቅርጽ ንድፍ ስራ በጥናት በፎርም ላይ መሰረት እንደሚያደርግ አስገንዝባቸው፡፡



የቅርጻቅርጽ ስራ ንድፍ የሚያሳይ ስዕል

## ልምምድ 3

መምህር/ት ከዚህ በኋላ ለተማሪዎች የተሰጠውን መመሪያ በመከተል እንዲሰሩ አድርጉ፡፡

1. በወረቀት ላይ በእርሳስ በአካባቢያቸው የሚያውቁትን እንደ ጀበና፣ስኒ፣ኩባያ፣ጽዋ፣እንስራ፣ ማሰሮ እና ከመሳሰሉት አንዱ መርጠው እንዲሰሩ አድርጉ፡፡
2. መምህር/ት ተማሪዎች የሰሩትን የቅርጻ ቅርጽ ስራ ንድፍ የእየአንዳንዱን በመመልከት ማስተካከል ባለባቸው ነገር ላይ ማስተካከያ ይስጡ፡፡
3. በመቀጠል በአካባቢያቹህ በሚገኝ የሸክላ አፈር ወይም ከሚያገኙት ነገር ላይ የሰሩትን ንድፍ እያዩ ቅርጻ ቅርጽ እንዲሰሩ ሁኔታ አመቻቹላቸው፡፡ መምህር ወይም መምህር/ት ተማሪዎች የሚሰሩትን ስዕል ወደ ፊት ለፊት ወጥተው ለክፍል ተማሪዎች

እንዲያሳዩ እና የሰሩትን ስራ በማህበረሰቡ ውስጥ የሚሰጠውን ጥቅም እንዲያብራሩ አበረታታቸው፡፡ በመቀጠል በሰሩት ስራ ላይ ጠንካራና ደካማ ጎናቸውን እንዲነጋገሩ አድርጉ፡፡

**ልምምድ 4**

መምህር/ት ተማሪዎች ከዚህ በታች የተሰጠውን የህትመት ስራ ንድፍ በማየት የተለያየ እርሳስ በመጠቀም እንዲነድፉ አድርግ፡፡ ከመንደፋቸው በፊት ከዚህ በኋላ የተሰጠውን የህትመት ንድፍ ስራ አሰራር እና ዘዴ ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው እንዲሰሩ በደንብ አስገንዝባቸው፡፡ ንድፍና የትምህርት ስራ ንድፍ አሰራር መካከል ጥብቅ ትስስር እንዳለቸው እና በሚሰራው የህተመት ስራ ሁሉ ውስጥ ንድፍ መሰረት እንደሆነ አስታውቃቸው፡፡ለምሳሌ፡- የእስቴንስል ህትመት ፣ የብሎክ ህትመት ፣ ኮላጅ፣ሞዛይክ ፣ፖስተር ሎጎ እና የመሳሰሉትን ለመስራት በቅድሚያ ለሚሰራው ስራ ዲዛይን መስራት አስፈላጊ መሆኑን መግለጽ፡፡ አብዛኛውን ግዜ ለህትመት ስራ ንድፍ ብርሃን እና ጨለማ ስራ ላይ በመመስረት እንደሆነ ገለጻ አድርግላቸው፡፡



## 2.3 የትያትር፣ የፎቶ እና የምስለ-ድምፅ (የቪድዮ) የሃሳብ ገለጻ

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ግዜ…………..8

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርእስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች

- የስነ-ትያትር፣ የፎቶና የምስለ-ድምፅ ሃሳብ ይገልፃሉ፡፡

### የይዘት ገለጻ

ይህ ርዕስ የሚያተኩረው ተማሪዎች የራሳቸውን ሀሳብ በትያትር እና በፊልም እንደሚገልጹ ለማድረግ ነው፡፡ አንድ ሰው የራሱን ሀሳብ በተለያየ መንገድ እንደዘፈን፣ስነ-ጽሁፍ፣በፎቶ፣እንዲሁም በትያትር እና በቪድዮ ሃሳባቸውን እንዲገልጹ ነው፡፡

ለምሳሌ፡- ሀሳባቸውን በትያትር መግለጽ ስንል የሰው ልጅ በአእምሮ ውስጥ ተከማችቶ ያለውን ሀሳብ በስነ ትያትር ለመግለጽ በውስጡ ይዞ ሀሳቡን ግን ወደ ፊጠራ ቀይሮ በስነ-ትያትር በመታገዝ መግለጽ ይቻላል፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴ

- በውይይት፣ በቡድን እና በጥንድ
- በማሳየት
- በገለጻ
- በጥያቄ እና መልስ
- በፕሮጀክት መልክ
- በልምምድ

### የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- የልምምድ ክፍል (የትያትር አዳራሽ)
- ለትያትር የሚውል እቃና አልባሳት

### የመምህሩ ድርሻ

የተሰጡትን ጥያቄ እና ድርጊቶች የግል ስራ፣የጥንድ ስራ፣የቡድን ስራ፣የክፍል ስራ፣የቤት ስራ እና በፕሮጀክት መልክ ሰርተው እንዲጨርሱ ምራቸው፡፡

- ተማሪዎች ሀሳባቸውን በሚገልጹበት መንገድ እንዲወያዩ አድርግ፡፡
- የተወያዩበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡

- ትያትርን በመጠቀም ሀሳባቸውን እንዲገልጹ አድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ እንዲሁም ብቃታቸው ሊመዘገብላቸው ይገባል፡፡ በደንብ ተገነዘብን ብለው እንዳይዘናጉ መከታተል እና ማበረታት ይገባል፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያመጡትን የክፍል ተማሪዎች ጋር ለማድረስ ተጨማሪ እረዳታ ይፈልጋሉ፡፡ የተለየ ትኩረት ለመስተት ተጨማሪ ትምህርት ሊሰጣቸው የገባል፡፡

## የተግባር 6 መልስ

1. በዚህ ተግባር ውስጥ ተማሪዎች የአይምሮአውን ሀሳብ በትያት ጽሁፍ እና በፊልም ቀይረው እነዲጽፉ በማድረግ እና በማበረታታት እንዲሁም ለሚሰሩት ስራ ትኩረት መስጠት፡፡

### የክትትል ምዘና

- በጥንድ እና በቡድን ውይይት
- በጥያቄ እና መልስ
- በግልና በቡድን በማሳየት
- በግል እና በቡድን ገለጻ
- በቤት ስራ
- በሙከራ
- በፈተና
- በስም መጥሪያ

## የምዕራፍ ሁለት መልመጃ መልስ

1.




2.




I. 1. እውነት 2. ሐሰት 3. ሐሰት 4.ሀሰት 5 እውነት 6. ሐሰት 7.ሐሰት 8.ሐሰት 9.እውነት 10. እውነት 11.ሐሰት 12.ሐሰት 13. እውነት

II. 1. D2.A 3.C 4.D 5.C 6.D 7.B

## ምዕራፍ 3 የስነጥበባት ታሪካዊና ባህላዊ ተጨባጭ ሁኔታ

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ግዜ …………….20

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-

- የባህል ሙዚቃ መሳሪያ እና ውዝዋዜ አይነት ለይተው ይገነዘባል፡፡
- የባህል ሙዚቃ እና ውዘወዋዜ መካከል ያለውን ልዩነት ለይተው ያውቃሉ፡፡
- ተረት ተረት እና ስነ-ጥበባት መሀል ያለውን ትስስር ያደንቃሉ፡፡
- ስነ-ጥበብ ተረት ተረትን ለመግለጽ ያለውን ጥቅም የገነዘባሉ፡፡
- ሥነ-ጥበብ እንዴት ተረት ተረትን ተጠቅሞ የትንትን ነገር እንደሚያሳይ ይገነዘባሉ፡፡
- ትርክትን ወደ ስነ-ትያትር ይቀይራሉ፡፡
- ታሪክን በስነ-ትያትር ይጽፋሉ፡፡

## የምዕራፉ ትልልቅ ርዕሶች

3.1. አፈ-ታሪክን በስነ-ጥበባት መግለፅ (ክፍለ ግዜ 5)

3.2. የባህል ሙዚቃ መሳሪያ እና ባህላዊ ውዝዋዜ (ክፍለ ግዜ 9)

3.3. የተውኔት ታሪክን በመጠቀም አስመስሎ መሳየት (ክፍለ ግዜ 6)

**መግቢያ**

ስነ-ትያትርም ሆነ ስነ ፊልም ለማዘጋጀት በመጀመሪያ ታሪክ ሊኖር ይገባል፡፡አንድ የስነ ቲያትር ሆነ የስነ-ፊልም ታሪክ ምንጭ ማግኘት እንችላለን፡፡ አንድ የታሪክ መገኛ ምንጭ የሆነው የማህበረሱ አፈ-ታሪክ ነው፡፡ በዚህ ርዕስም የማህበረሰቡ አፈ ታሪክ ውስጥ ትርክት ወይም ተረት ተረትን በምንኖርበት አካባሚ በማጥናት ስነ-ትያትርን በመጠቀም አሳዩ፡፡ ከዚህ ሌላ ቤዝ ክሌፍ እና ትሬብል ክሌቭ እነዲሁም ከፍ ያለ እና ዝቅ ያለ የሙዚቃ ድምጽ፣ጥቀሙን እና በሙዚቃ እስታፍ ላይ እንዴት እንደምታዜሙ ተምራችኋል፡፡ እንዲሁም የባህል ሙዚቃ መሳሪያ እንዴት እንደሚሰራና አጨዋወቱን፣ፍቺውን እና ጥቅሙን እና የባህል ውዝዋዜን ትማራላችሁ፡፡

ማንኛውም ባህል የራሱ ተረት ተረት አለው፡፡ ተረት ተረት ባህል፣ታሪክን፣እሴት የብሂሩ ጀግናና በአንድ ማህብረሰብ ውስጥ ለማሳየት በጣም ይጠቅማል፡፡ ተረት ተረት ስነ-ጥበብን የሚያሳይ ነው፡፡

## 3.1 ተረት ተረት ስነ-ትያትርን በመተቀም ማሳየት

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ግዜ…………..5

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎነጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች፡-

- ትርካን ወደ ስነ-ቲያትር በመቀየር ያሳያሉ፡፡

### የይዘቱ አንኳር ነጥብ

- ትርካን በስነ-ቲያትር በመጠቀም ማሳየት

### የይዘት መገለጫ

ይህ ርዕስ ትርክት እና ተረት ተረትን ወደ ድርሰት፣ስነ-ትያትር፣ስነ-ፊልም እንዲቀይሩ ያስተምራል፡፡ በተሰጠው ምሳሌ ላይ በመመስረት አፈ-ታሪክ ውስጥ ስነ-ትያትር እና ስነ-ፊልምን ማቅረብ እንደሚቻል ወደ ተውኔት በመቀየር እንዲያሳዩ አድርግ፡፡

በተማሪው መጽሀፍ ላይ የተሰጠው አፈ-ታሪክ በተውኔት መልክ፡-

### ውሻ እና አህያ

በድሮ ግዜ አህያ እና ውሻ በጌታቸው ቤት ይኖሩ ነበር፡፡ አህያዋ የጌታዋ ሸክም ስለሰለቻት ተነስተን እንጥፋ ብላ ውሻዋን ጠየቀች፡፡ ውሻዋ ግን ታገሺ ብላ መከረቻት፡፡ አህያዋ መታገስ አልቻለችም፡፡ አንድ ቀን አሕያዋ ልትጠፋ ስትነሳ ውሻዋም ከጓደኛዋ መቅረት ስላልፈለገች ተከተለቻት፡፡ እየሄዱ እያሉ ሲመሽባቸው ለምለም ሳር አግኝተው አረፉ፡፡ አህያዋ ሳሩን በልታ በልታ ጠገበች፡፡ ውሻዋም አመድ አግኝታ ላሰች፡፡ ሊነጋጋ ሲል አህያዋ ጠግባ እጮሃለሁ አለች፡፡ ውሻዋ ግን ፈርታ እንዳትጮሂ ብላ ከለከለቻት፡፡ አህያዋ እንቢ ብላ ጮኸች ለሁለተኛ ግዜ ደግማ ጮኸች በሶስተኛው ጅብ አህያዋን ይዞ አንጀቷን ዘርግፎ ገደላት፡፡ ውሻዋም ጥሻ ውስጥ ተደበቀች፡፡ ጅብ ሲያያት ከዚህ ምን ትሰሪያለሽ ብሎ ጠያቃት፡፡ ጌታዬ አደን ልናድን ነው የወጣነው አለች፡፡ ጅብም ነይ አሁን ቶሎ ይህንን ስጋ ብልት በብልት አውጭ እና ልቡን አስቀምጭልኝ አለ፡፡ ውሻዋም ይህንን እየሰራች እያለ ልቡን ወስዳ ዋጠች፡፡ ጅብም ተመልሶ ያወጣሽውን የአህያ ልብ ስጪኝ ሲላት ውሻዋም ምነው ጌታዬ! አህያዋ ልብ ቢኖራት ኖሮ ለምን ጮሃ ትበላ ነበር አለችው ይባላል፡፡

## የመማር ማስተማር ዘዴ

- በውይይት፣ በቡድን እና በጥንድ
- በማሳየት
- በገለጻ
- በጥያቄ እና መልስ
- በፕሮጀክት መልክ
- በልምምድ

## የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- የልምምድ ክፍል (የትያትር አዳራሽ)
- ለትያትር የሚውል እቃና አልባሳት

## የመምህሩ ድርሻ

የተሰጡትን ጥያቄ እና ድርጊቶች የግል ስራ፣የጥንድ ስራ፣የቡድን ስራ፣የክፍል ስራ፣የቤት ስራ እና በፕሮጀክት መልክ ሰርተው እንዲጨርሱ ምራቸው፡፡

- የተሰጡትን ድርጊቶች እና ጥያቄዎች እንደ ግል ስራ፣የጥንድ ስራ፣የቡድን ስራ፣የቤት ስራ እና ፕሮጀክት እንዲሰሩ አድርግ፡፡
- ስለ አፈ-ታሪክ አስመልክቶ በአለፈው ትምህርት ውስጥ የተማሩትን እንዲያስታውሱ አድርግ፡፡
- በተማሪዎች መጻፍ ውስጥ የተጻፈውን አፈ-ታሪክ ድርሻ በመውሰድ በቲያትር መልክ እንዲያቀርቡ አድርጉ፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ እንዲሁም ብቃታቸው ሊመዘገብላቸው ይገባል፡፡ በደንብ ተገነዘብን ብለው እንዳይዘናጉ መከታተል እና ማበረታት ይገባል፡፡
- ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ያመጡትን የክፍል ተማሪዎች ጋር ለማድረስ ተጨማሪ እረዳታ ይፈልጋሉ፡፡ የተለየ ትኩረት ለመስተት ተጨማሪ ትምህርት ሊሰጣቸው የገባል፡፡

## የተግባር 1 መልስ

1. አንድ የትያቲር ስራ ለቲያትር የሚሆነውን ሀሳብ ከመፍጠር ይጀምራል፡፡ ይህም ሀሳብ ከመፍጠር ይጀምራል፡፡ ይህም ሀሳብ ጸሀፊው ገጠመኝን ልምድን እና ከተለያዩ ጽሁፎች እና የማህበረሰቡ የኑሮ ሁኔታ ከመሰሰሉት ነገሮች ሊያገኝ ይችላል፡፡ ለቲያትር የሚሆን ሀሳብ ከተዘጋጀ በኋላ የተውኔት ጽሁፍ በመቀየር ቲያትር ተዘጋጅቶ ለተመልካች ይቀርባል፡፡
2. ተማሪዎች የሚያውቁትን አፈ-ታሪክ ከተነጋገሩ በኋላ በስነ-ቲያትር መልክ ማቅረብ የሚችሉትን እንዲዘጋጅ አድርጉ፡፡

**ተከታታይ ምዘና ዘዴ**

- የጥንድ እና የቡድን ውይይር
- ጥያቄ እና መልስ
- በግል እና በቡድን በማሳየት
- የግል እና የቡድን ገለጻ
- የቤት ስራ
- ሙከራ
- ፈተና
- ስም መጠሪያ እና የመሳሰሉት

## 3.2 የባህል ሙዚቃ መሳሪያ እና የባህል ውዝዋዜ

### 3.1.1.የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች

በዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ግዜ............ 2

ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ የሚገባቸው የመማር ብቃት

- በዚህ ትምህርት መጨረሻ ላይ ተማሪዎች
- የሙዚቃ መሳሪያዎች ክፍፍል ይገልጻሉ፡፡
- የባህል ሙዚቃ መሳሪያ አይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፡፡

### የመማር ማስተማር ዘዴ

- ቀድሞ በማሳየት
- የጥንድ የቡድን እና የክፍል ውይይት
- ገለጻ
- ጥያቄ እና መልስ
- ልምምድ
- የትምህር

## የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች

- ለዚህ ትምህርት ርዕስ የሚውል የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች
- የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች
- የባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች ስዕል

### የመምህሩ ድርሻ

- ተማሪዎችን ስለከፍተኛ እና ዝቅተኛ ድምጽ በመጠየቅ እንዲያብራሩ በማድረግ ትምህርቱን ማስጀመር ይቻላል፡፡
- ተማሪዎች ስለ ባህል የሙዚቃ መሳሪያዎች በጥንድ እና በቡድን እንዲወያዩ በማድረግ የውይይታቸውን ውጤት ለክፍል እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡
- በዚህ ርዕስ ስር የተሰጠውን ድርጊት የተማሪዎችን እውቀት እና ችሎታ ለማወቅ ስለሚረዳ ተማሪዎችን በማነሳሳት ወደ ገለጻ ከመግባትህ በፊት እንዲወያዩ አድርግ፡፡

# የተከታታይ ምዘና ዘዴዎች

- ለስራቸው ትክክለኛ የሆነ ግብረ መልስ በሰአቱ መስጠት፡፡

  ተማሪዎች ቢያንስ ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በላይ ካስመዘገቡ ሊበረታቱ ይገባል፡፡

እንዲሁም ጥንካሪያቸው ሊመዘገብላቸው ይገባል፡፡ ሁሉን አወቅን ብለው መሻሻልን እንዳያቆሙ ሊበረታቱ ይገባል፡፡ የተማሪውን ስራ አንድ በአንድ መዝግብላቸው፡፡

ተማሪዎች ቢያን ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት በታች ከስመዘገቡ ሌሌው ተማሪ ጋር ለማድረስ ተጨማሪ ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ ሰለዚህ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶአቸው ተጨማሪ ድጋፍ በመስጠት በእረፍት ሰዓት ወይም በትምህርቱ መጨረሻ ላይ ሊረዱ ይገባል፡፡

መመህር/ት ተማሪዎች በተግባር ሁለት በቡድን በቡድን ሆነው በአካባቢያቸው የሚገኘውን የበህል ሙዚቃ ሰርተው እንዲመጡ አድርግ፡፡

## ሀ. የምት የባህል ሙዚቃ መሳሪያዎች

ለዚህ ትምህርት ርዕስ የተሰጠው ክፍለ ጊዜ………………2

ተማሪዎች ቢያን ሊጎናጸፉ ከሚገባቸው የመማር ብቃት፡-

በዚህ ርዕስ መጨረሻ ላይ ተማሪዎች ፡

- የምት የሙዚቃ መሳሪያ ምንነት ይገልጻሉ፡፡
